# ሁለት አገሮች፣ አንድ ማህበረ-ሰብ፤
# የኮንፌደረሽን ጉዳና ለኢትዮጵያና ለኤርትራ


ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)

ብረመን ዩኒቨርሲቲ፣ ጀርመን



*የኢትዮጵያና ኤርትራ ወዳጅነት ኮንፈረንስ*

*ዋሺንግተን፣ ዲ. ሲ. ሚያዝያ (አፕሪል) 22፡ 2018*

# ማብራሪያና ምስጋና

የሚከተለው ጽሁፍ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወዳጅነት መድረክ ሚያዝያ (አፕሪል) 22 2018 ዓ. ም. በዋሺንግተን ከተማ ላደራጀው ዓመታዊ ኮንፈረንስ የተዘጋጀ ነው፡፡ በኮንፈረንሱ ያቀረብኩት ንግግር፣ ያኔ እንደገለጽኩት፣ የዚሁ ጽሁፍ አጠር ያለ ሀተታ ነበር፡፡ ጽሁፉ በሙሉ በተለያዩ ድህረገጾች እንደሚወጣ በንግግሬ ጠቅሼ ነበር፡፡ ባልኩት መሰረት ሙሉው ጽሁፍ እነሆ፡፡

ይህንን ጽሁፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ስማቸው መጥቀስ የማያስፈልግ ወዳጆቼ አስተያየቶች በመለገስና በሌሎች የተለያዩ መንገዶች ተባብረውኛል፡፡ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወዳጅነት መድረክ ኮንፈረንሱን አዘጋጅቶ በዚህ ጽሁፍ አማካይነት ሃሳቤን ለማሰራጨት ዕድል ሰጥቶኛል፡፡ ለተባበሩኝ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በዚሁ ጽሁፍ ላይ የሰፈረውን ይዘት በሚመለከት ሃላፊነት የምወስደው እኔ ራሴ ብቻ መሆኔን ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ተስፋጽዮን መድሃኔ
ብረመን ዩኒቨርስቲ፣ ጀርመን፡፡
ግንቦት (መይ) 2018

# ሁለት አገሮች፡ አንድ ማህበረ-ሰብ፤ የኮንፌደረሽን ጕዳና ለኢትዮጵያና ለኤርትራ

ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)
ብረመን ዩኒቨርስቲ፣ ጀርመን

በዚሁ የኢትዮጵያና ኤርትራ የወዳጅነት መድረክ የሁለቱ አገሮች ዝምድና ምን ይሁን የሚለውን ጥያቄ ደጋግመን ጐብኝተነዋል፡፡ በ2009 እና በ2010 በሳንሆዘ ከተማ እኔና ወንድሜ ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ የተሳተፍንባቸው ስብሰባዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ተካሂደዋል፤ ውጤታቸውም አመርቂ ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡

ኤርትራ ተገንጥላ የተለየች አገር ከሆነች አንስቶ ለሁለቱ አገሮቻችን የሚበጀው ዝምድና ኮንፌደረሽን ነው የሚለውን ዕይታ ሳስተጋባ ነበር፡፡ የኮንፌደረሽንን ሃሳብ የሚያራምዱ ጥናቶችም በተለያዩ ስብሰባዎችና በጽሁፍ መልክ አቅርቤአለሁ[1]፡፡

የኮንፌደረሽን ሃሳብን የሚቃወሙ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ነበሩ፤ ባሁኑ ወቅት ግን ስለ ኮንፌደረሽን ያለው አመለካከት እየተሻለ መጥቷል፡፡ በመሰረቱ አሁን ስለ ኮንፌደረሽን፡ ገና በቂ ባይሆንም፡ ከበፊቱ የላቀ ግንዛቤ ያለ ይመስላል፡፡ ኮንፌደረሽን ለሚለው ሃሳብ የነበሩት ዕንቅፋቶች እየደከሙ መጥቷል፡፡

የሁለቱ አገሮች ተነጣጥሎ መኖር ካለው ዕውነታ ጋር የማይጣጣም መሆኑ ባሁኑ ጊዜ በተግባር እየታየ ነው፡፡ ከአስር ዓመት በፊት ባሳተምኩት አነስ ያለ መፅሃፍ የጠቀስኩት አንድ ፀሃፊ ያለው ይህንን ነጥብ የሚመለከት ሃሳብ አለ፡፡ ፀሃፊው ኤርትራና ኢትዮጵያ ተለያይተዋል እንጂ አልተፋቱም ሲል መጐተ፡፡ እኔ ግን የፀሃፊው በጎ መንፈስ ቢገባኝም ነገሩ የተገላቢጦሽ መሆኑን ለማሳየት ሞከርኩ፤ ማለቴ፡ እውነቱን ለመናገር፡ ኤርትራና ኢትዮጵያ በይፋ ተፋትተዋል፤ ኤርትራ ሉዓላዊ አገር ተብላ፡ ፀረህዝብ ቢሆንም፡ የራስዋ መንግስት አላት፤ ከ1993 አንስታ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሆናለች፤ ከብዙ አገሮች ጋርም ዲፕሎማስያዊ ግንኙነት አላት፡፡ በህግ የኢትዮጵያ አካል የሚያደርጋት ዝምድና አብቅቷል፡፡

ኢትዮጵያና ኤርትራ በይፋ ቢፋቱም በመሬት ላይ ያለው ዕውነታ የሚመሰክረው በተግባር ያልተለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ ኤርትራውያን ገና በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ፤ ከኢትዮጵያውያን ጋር ተሳስረዋል፡ ተዛምደዋል፡፡ በስደት ያሉ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን በወንድማማችነት ይኖራሉ.፤ አንዳንዶቹማ ተጋብተው ትዳር እየመሰረቱ ናቸው፡፡ በባህል ረገድ የነበረው ግኑኝነታችንና ጋራነታችን ያው እንደቀጠለ ነው፡፡ በይፋዊ

1. ካሁን በፊት በእንግሊዝኛ ካሳተምኳቸው ድርሰቶችና መጣጥፎች ብዙ ሃሳቦች ወስጄ በዚህ ፅሁፍ አስፍሬያለሁ፡፡

ፍቺ ምክንያት ኤርትራም ኢትዮጵያም ብዙ ችግር እያሳለፉ ናቸው፤ ይኸም ለራሱ አለመለያየት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ተነስቼ፡ እኔ ሁለቱ አገሮች በተግባር አልተለያዩም ብቻ ሳይሆን፡ እንድያውም ሊለያዩ አይችሉም ማለት እደፍራለሁ፡፡

ኮንፈደረሽን አስፈላጊ ይሁን እንጂ አሁኑኑ እውን ሊሆን ይችላል ማለት አይደለም፡፡ አሁን ያሉት መንግስታት ለኮንፈደረሽን ፍላጎቱም ሆነ ብቃቱ የላቸውም፡፡ በሁለቱ አገሮችና ዝምድናቸውን በተመለከተ፡ ቆየት ብዬ እንደምገልፀው፡ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች አሉ፡፡

፩

ስለ ኮንፈደረሽን ትርጉም ያለው ግንዛቤ አሁን የተሻለ ቢሆን እንኳን ገና በቂ አይደለም፡፡ የኮንፈደረሽን ትርጉም ወይም ፅንሰ ሃሳብ በኤርትራና ኢትዮጵያ ሁኔታ ደመቅ ያለ ተራ ያላቸው ጉኖች አሉት፡፡ ኮንፈደረሽን ምን ማለት ነው? ባጭሩ ሲገለፅ ኮንፈደረሽን ማለት የሁለት ወይም በቁጥር ከዚያ የበለጡ ሉዓላዊ አገሮች ህብረት (ዩኒዮን) ማለት ነው፡፡ አባል አገሮቹ ለህብረቱ የተወሰነ ሃይል ወይም ስልጣን ይሰጡታል፤ ህብረቱ እነርሱ ካስተላለፉለት በላይ ሃይል ወይም ስልጣን የለውም፡፡

አንዳንዱ ኮንፈደረሽን ለአንድ የተወሰነ የጋራ ጉዳይ ለማጠናቀቅ የሚቋቋም ትስስር ነው፡፡ ይህ ብዙውን ጊዜ አገሮች ከወራሪዎች ለመከላከል የሚያቆሙት ጊዜያዊ ህብረት ነበር፡፡ የጋራው ችግር - ወራር ይሁን ሌላ - ካቆመ በኋላ ኮንፈደረሽኑ ያበቃል፡፡ እንዲህ ዓይነት ኮንፈደረሽን ወደ ፈደረሽን ይሁን ወደ ሌላ ዓይነት ውህደት ሊመራ አይችልም፡፡

ሌላው ዓይነት ኮንፈደረሽን ደግሞ ለተወሰነ ጉዳይ ተብሎ የሚቋቋም ትብብር ሳይሆን በይዘቱ ሰፊ ወይም አጠቃላይ የሆነ ነው፡፡ ጊዜያዊ ሳይሆን ቀጣይ ነው፡፡ ይዘቱ እየጨመረ ሂዶ የአገሮቹ ዝምድና እያደገ፡ እየሰጠመ እና እየጠነከረ ይመጣል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ኮንፈደረሽን እስከ ፈደረሽን፡ እስከ ሙሉ ውህደትም ሊደርስ ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነት ኮንፈደረሽን አብነቶች በአሜሪካና በጀርመን ታሪክ የታዩት ናቸው፡፡

ፈደረሽን ግን ከኮንፈደረሽን የተለየ ነው፡፡ በፈደረሽን የሚተሳሰሩት አካላት ወይም አገሮች ሉዓላዊ አይደሉም፤ ለማእከላዊው መንግስት ተገዢ (ማለት የበታች) ናቸው፡፡ አገሮቹ በሙሉ ተደምረው የሚያቆሙት አንድ አካል ነው ሉዓላዊው አገር፡፡

የኮንፈደረሽን ዝምድና በተለያዩ ስሞች ነው የሚጠራው፤ ለምሳሌ ማህበረ-ሰብ (አውሮጳ)፡ህብረት (አውሮጳ)፡ የነፃ ሀገሮች ኮሞንወልዝ (ሩሲያና ሌሎች)፡ ሊግ (በተለይ በድሮ ዘመን) ወዘተ፡፡. የዝምድናው ይዘትም ይለያያል፤ አባል አገሮቹ የተስማሙበት ነው የሚሆነው፡፡ በዘመናችን ግን አብዛኛውን ጊዜ ኮንፈደረሽን ሲባል መከላከያን ውጭ ጉዳይንና አለማቀፋዊ ንግድን በተመለከተ የጋራ ተቋማትና የጋራ ፖሊሲ ይኖሩታል፡፡ እንዲሁም በአውሮጳ ህብረት ታሪክ እንደታየው የአገሮቹ ድንበሮች በበለጠ ክፍት እየሆኑ

መጥተው ዜጎቹ በተዛመዱት አገሮች ሁሉ ሊኖሩ፣ ሊሰሩ፣ ሊነግዱ፣ እና ንብረት ሊያፈሩ ይችላሉ ማለት ነው[2]፡፡

የአንድ ኮንፌደረሽን ግብ ዝምድናው እያደገ መጥቶ በሂደት እስከ ሙሉ ውህደት መድረስ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ግን ግቡ ምን እንደሆነ በስምምነቱ ይጠቀሳል ማለት አይደለም፡፡ አንዳንዴ ግቡ ምን እንደሆነ ሳይጠቀስ ከይዘቱ መገንዘብ ይቻላል[3]፡፡

ኮንፌደራላዊ ዝምድና አስተማማኝ ጠንካራና ታዳጊ የሚሆነው የአወቃቀሩ ሂደት ህዝባዊ መሰረት ያለው ሲሆን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ኮንፌደራላዊ ዝምድና በህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ ይህ ማለት ባጭሩ ኮንፌደረሽን ማቋቋም የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አንድ ክስተት ወይም ሁኔታ ነው፡፡ ህዝቡ ይህንን መብት የሚገለገልበት ደግሞ ብዙውን ጊዜ በረፈረንደም ወይም ህዝበ-ውሳኔ ነው፡፡

፪

የራስን ዕድል በራስ መወሰን ማለት ምንድን ነው? ይህ ማለት በአንድ ጉዳይ ህዝቡ ይጠቅመኛል ብሎ የሚያምነውን ሁናቴ ይገልጻል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መታወቅ ያለባቸው ሁለት ነጥቦች አሉ፡፡

1. የራስን ዕድል በራስ መወሰን አንድ ዘዴ ብቻ ነው፤ ሂዶ-ሂዶ መሰረታዊ ግቦች ላይ የሚያደርስ መንገድ ነው፡፡ በፖለቲካ ረገድ ህዝቡ ለምሳሌ ከመገንጠልና ከውህደት ምርጫዉን በረፈረንደም ይገልጻል፡፡ ይህ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ነው፡፡ በረፈረንድሙ የተመረጠ ሁናቴ ግን ከበስተጀርባው ያለውን ራዕይ ወይም ዓላማ የሚያገለግል እንጂ ለራሱ የመጨረሻ ወይም ዋና ግብ አይደለም፡፡

ይህንን ነጥብ በበለጠ ለመረዳት በዋና ግብ ወይም ራዕይና በስትራተጂ መሃከል ያለውን ዝምድና ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

ዋና ግብ ወይም ራዕይ ማለት፡ በቀላል አነጋገር፡ የመጨረሻው ወይም መሰረታዊ ዓላማ ማለት ነው[4]፡፡ ይኸውም የህዝቡን ኑሮ ወይም የአኗኗር ሁኔታ ማሻሻልና ማሳደግ፤ በአጭሩ ሁለንተናዊ የህይወት እርካታ ነው፡፡ ይህ ሰው ሲባል በህይወት እንዲሚላለት የሚያስፈልግ

---

2 . John A. Akec, "To confederate or not to confederate is a matter of strategy", Sudan Tribune, Septemvber 14, 2010, < http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=36261 > accessed on January 10, 2018, ; John A. Akec, "Confederation; A Better Tool for Good Neighborliness and Prosperous Relationship between Sudan and South Sudan", *UNISCI Discussion Papers*, Nr. 33, October 2013 (Madrid Spain), p. 158 <http://www.redalyc.org/articulo.oa?id=76728723011 >; Mahmoud A. Suleiman, "Confederal System for Sudan", Sudan Tribune, January 8, 2008 http://sudantribune.com/spip.php?page=imprimable&id_article=25592 accessed on Janury 10, 2018

3 . University of Pretoria, "Supranationalism in the African context; A critical look at past and present attempts at building supranational organizations in Africa", p. 115, <https://repository.up.ac.za/bitstream/handle/2263/28573/02chapter3.pdf?sequence=3>

4 . John A. Akec, "To confederate or not to confederate is a matter of strategy", op. cit.

ሁሉን የሚመለከት ሆኖ፡ ማህበረ ኤኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ እና ሰብአዊ መብቶችን በሙሉ፡ ከሁሉም በላይ በህይወት የመኖር መብትን ያካተተ ነው፡፡ ይህ አንድ ሰው ለጤናማ ህይወት የሚፈለገው ሁሉ እንዲሟላለት፡ ቤተ ሰብ ለመመስረትና ለመደሰት፡ ደህንነቱ እንዲጠበቅ፡ የንብረት ባለቤት የመሆን፡ የመማር፡ የመናገር የመምረጥ የመመረጥና የመንቀሳቀስ መብቶቹን ወዘተ. ያጠቃለለ ነው፡፡

ስትራተጂ ወይም ብልሃት ማለት ግን የመጨረሻ ግቦችን ለማሟላት ያገለግላል ተብሎ የተወሰነ ሁናቴ ማለት ነው[5]፡፡ ለምሳሌ የህዝቡ ምርጫ አንድነት ከሆነ አንድነቱ የመጨረሻ ግብ አይደለም፤ ግቦቹን ለማሟላት የሚያገለግል ስትራተጂ ወይም የተመረጠ ብልሃት ብቻ ነው[6]፡፡ እንደዚሁም መገንጠል እና ተገንጥሎ ሉዓላዊ አገር መሆን አንድ ስትራተጂ ወይም ብልሃት ነው፡፡ ይህ ስትራተጂ ሲመረጥ የመጨረሻ ግቦችን ያሟላል ተብሎ ስለታመነበት ነው ወይ መሆን ይገባል፡፡

ስለዚህም ሉዓላዊነት ጨርሶ የማይነካ ወይም የማይደፈር ነው ማለት አይደለም፡፡ ሱዳናዊው ምሁር፡ ፕሮፌሰር ዓብዱላሂ አን ናዒም፡ እንደፃፈው ሉዓላዊነት "በቀላሉ ሊደፈር ወይም ሊጣስ አይገባም"፤ ነገር ግን ከበስተጀርባው ያለውን ግብ ለማጨናገፍ ማገልገል የለበትም[7]፡፡ በሌላ አነጋገር፡ በሉዓላዊነት ስም መንግስታት ህዝቦቻቸውን መጨቆንና በማንኛውም ረገድ መጉዳት አይገባቸውም፤ ይህንን በማድረግ የሉዓላዊነትን መሰረታዊ ግብ ሲያጠቁ ሌሎች መንግስታት የህዝቦቹን መብት ለማስከበር የሚደረገውን ጥረት ቢደግፉ ሉዓላዊነትን ጥሳችኋል ተብለው አይወቀሱም፡፡

2. የተመረጠው ስትራተጂ - ለምሳሌ መገንጠል - በሂደት ግቡን የማያሟላ ወይም ለማሟላት የማይችል ሆኖ ከተገኘ፡ ወይም ሁኔታው ተለውጦ ዝምድናው መስተካከል አለበት ከተባለ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፤ ይህ ማለት እንደገና ረፈረንደም ተካሂዶ ይሁን ወይም በሌላ መልክ ህዝቡ ፍላጎቱን መልሶ ይገልጻል ማለት ነው፡፡

ከስትራተጂ ጋር በተያያዘ ነፃነት - ማለት ፖለቲካዊ ነፃነት - የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን ፅንሰ-ሃሳብ በተመለከተ የተሳሳተ ግንዛቤ አለ፡፡ ብዙ ወይንም አብዛኛው ያገራችን ሰው ነፃነት ሲባል ከመገንጠል ጋር ብቻ ያያይዘዋል፡፡ ሙሉ አንድነት፡ ፌደረሽን ወዘተ. የህዝቡ ፍላጎት ቢሆንም በልማድ ነፃነት ተብሎ አይገለፅም፡፡ ይህ መሰረታዊ ስህተት ነው፡፡ አንድ አገር ወይም ህዝብ ከሌሎች ጋር የሚኖረውን ዝምድና በተመለከተ ነፃነት ሲባል ህዝቡ በሙሉ ፍላጎት የመረጠው ወይም የተቀበለው ሁናቴ (status) ማለት ነው፡፡ ህዝቡ ያለ ምንም ተፅእኖ ወይም ማጭበርበር የመረጠው

5 . ስትራተጂው የሚጠናቀቀው አመርቂ ተብሎ የተመረጠውን አካሄድ በመጠቀም ነው፡፡ ይህ አካሄድ ዘዴ (ታክቲክ) ይባላል፡፡ዝኒ ከማሁ

6 . የአንድነትን ምርጫ በተመለከተ የሚከተለውን ዕይ፡፡ Francis M. Deng, "Prospects for Reconciling Self-Determination with Unity in Sudan", (Khartoum,: Symposium on Unity and Self-Determination, November 2, 2009) <http://www.un.org/en/preventgenocide/adviser/pdf/SAPG%20statement%20in%20Khartoum.%20Nov%2009.pdf > accessed on March 7, 2018

7 . Abdullahi Ahmed An-Na'im, "Third World Perspectives", in Elizabeth Ferris (ed), *The Challenge to Intervene: A New Role for the United Nations*, (Uppsala: Life & Peace Institute, 1992), p. 145

ወይም የተቀበለው አህዳዊ ውህደት ይሁን ፌደረሽን ይሁን ኮንፌደረሽን ይሁን ወይንም መገንጠል ሁሉ ፖለቲካዊ ነፃነት ነው፡፡ አንድነት ሲባል መልኩ አሃዳዊ ይሁን ፌደራላዊ፡ እንደ ባርነት አድርጎ ማቅረብ ትልቅ በደል ነው፡፡ እንዲህ ከሆነማ የስኮትላንድ ህዝብ ከጥቂት ዓመታት በፊት በነፃ ረፈረንደም መገንጠልን ተቃውሞ ከእንግሊዝ አገር ጋር በአንድነት ለመቀጠል በመወሰኑ ባርነትን መረጠ ሊባል ነው፡፡ እንደዚሁም የኮቤክ ህዝብ ደጋግሞ በነፃ ረፈረንደም መገንጠል አንፈልግም ብሎ ከካናዳ ጋር በአንድነት መቀጠሉ ባርነትን መረጠ ሊባል ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ዋናው ጥያቄ የተመረጠው ስትራተጂ በህዝቡ ነፃ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ህዝቡ ያለ ምንም ተፅእኖ ወይም ማጭበርበር የመረጠው እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ውጤት ነፃነት ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ህዝቡ በተፅዕኖ ወይም በማታለል ወይም ተገድዶ የተቀበለው ከሆነ አንድነት ይሁን መገንጠል ነፃነት አይደለም፡፡

ስትራተጂ የመጨረሻውን ግብ ለማሟላት የሚያገለግል ብልሃት ነው ከሚለው ሃቅ ተነስተን ስለ ኮንፌደረሽን ልንገነዘበው የሚገባ መሰረታዊ ነጥብ አለ፡፡ ኮንፌደረሽን -ለተወሰነ ጉዳይ የሚቋቋም ጊዜያዊ ትብብር ዓይነቱ ካልሆነ በስተቀር- በይዘት ባለበት የሚረጋ ወይም የማይለወጥ አይደለም፡፡ ይሻሻላል፤ ይቀየራል፡፡ አንዳንዱማ በየጊዜው የሚታደስ ኮንፌደረሽን ነው[8]፡፡ Renewable confederation ይባላል፡፡ ለምሳሌ የኮንፌደረሽኑ ዕድሜ አምስት ዓመት ነው ተብሎ ይደነገጋል፡፡ ይህ ግን ከአምስት ዓመት በኋላ ግንኙነቱ ያከትማል ማለት አይደለም፡፡ ይህ ማለት ከአምስት ዓመት በኋላ የኮንፌደረሽኑ ዝምድና ምን ያህል እንዳገለገለ፡ እንደስትራተጂ ዋናውን ግብ ወይም ራዕይ ለማሟላት ምን ያህል እንደረዳ ይገመገማል ማለት ነው፡፡ በዚሁም መሰረት የኮንፌደረሽኑ ይዘት ይሻሻላል፡ ያድጋል፡፡ ህዝቡ እንደገና በነጻ ረፈረንደም የታደሰውን ኮንፌደረሽን ወይም ያጸድቃል ወይም ይቃወማል፡፡ ረፈረንደም በየጊዜው እየተደጋገመ ኮንፌደረሽኑ ፌደረሽን እስከ መሆን ድረስ ሊያድግ ይችላል፡፡ የአውሮጳ ህብረት ይህንን ሂደት ተከትሎ ነው እያደገ መጥቶ አሁን ፌደረሽን ለመሆን ተቃርቦ ያለው፡፡

በሌላው በኩል ደግሞ አንድ አባል አገር ከኮንፌደረሽኑ በቂ በሆነ መጠን አልተጠቀምኩም ብሎ ከህብረቱ ሊወጣ ይችላል፡፡ ለምሳሌ እንግሊዝ አገር በ1973 የአውሮጳ ህብረት አባል ሆነች፤ ባለፈው ዓመት ደግሞ ረፈረንደም ተካሂዶ ጥቅምዋን በበለጠ ለማራመድ ብላ ከህብረቱ ወጣች፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ኮንፌደረሽን የሉዓላዊ አገሮች ህብረት በመሆኑ ነው፡፡

## ፫

እንኳንስ ኢትዮጵያና ኤርትራ የአፍሪቃ ቀንድ አገሮች በሙሉ በኮንፌደረሽን ሊተሳሰሩ ሁኔታቸው ያስችላል የሚል አስተያየት ያላቸው ምሁራን አሉ፡፡ በአፍሪቃ ደረጃም

---

8 . John A. Akec, "A call for renewable confederation in post 2011 Sudan", Sudan Tribune June 8, 2010 available online at <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=35326>

ኮንፌደረሽን ቢያንስ እንደ ራዕይ ይታሰባል[9]፡፡ በተጨባጭ ኮንፌደረሽንን አስመልክቶ ውይይት የተካሄደበት ጉዳይ ግን የደቡብ ሱዳን ጥያቄ ነበር[10]፡፡ ሞዋቹ ዶክ. ጆን ጋራንግ የኮንፌደረሽን ስርዓት ለሱዳን በጠቅላላ መፍትሄ ይሆናል የሚል አቋም ነበረው፡፡ በቂ ድጋፍ አላገኘም[11]፤ ስለዚህም በረፈረንደም ሂደት ደቡብ ሱዳን ተገነጠለ፡፡

ኮንፌደረሽን በቀጠናችን ምን ያህል ስኬታማ ይሆናል በሚል ጥያቄ ላይ የሃሳብ ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡ አንድ ነገር ግን ግልፅ ነው፡፡ ከአፍሪቃ ቀንድ አገሮች ሁሉ በኮንፌደረሽን ለመተሳሰር ታሪካቸውና ሁኔታቸው በእጅጉ የሚፈቅድላቸው ወይም የሚያስችላቸው ኢትዮጵያና ኤርትራ ናቸው፡፡ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና ባላቸው የተፈጥሮ ፀጋ እርስ በርሳቸው የሚፈላለጉ ወይም ተደጋጋፊ (ኮምፕሊመንታሪ) ናቸው፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ መሬትና ውሃ ሲኖራት፡ ኤርትራ ደግሞ አስፈላጊ የሆኑ የባህር በሮች አሉዋት፤ በጠቅላላው አነጋገር ህዝቦቹ አንድ ዘር ወይም ነገድ ናቸው፤ ባህሎቻቸው በአብዛኛው አንድ ካለበለዚያ እጅግ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በሁለቱ አገሮች ዋናዎቹ ሃይማኖቶች ክርስትናና እስልምና ናቸው፤ በሁለቱም የክርስትያኑና የእስላሙ ቁጥር ተመጣጣኝ ነው፡፡ ድንበሮቻቸው አውሮጳዊ ቅኝ ግዛት የፈጠረው ነው፤ ሁለቱ አገሮች "የነገድ ወይም የባህል ክልሎች" አይደሉም፡፡ ህዝቦቹ ታሪካቸው በአብዛኛው አንድ ነው፤ እርስ በርሳቸው የተዋወቃሉ፡ ይግባባሉ፤ ለዘመናት አብረው ኖሯል፡ ተዛምዷል ተዋልደዋል፡፡

እነዚህ ሁሉ ኮንፌደረሽንን የሚቻል የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በተቀራኒው ደግሞ ለኮንፌደረሽን ዕንቅፋት የሚሆኑ ወይም ኮንፌደረሽንን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ነገሮች አሉ፡፡ አንዳንዱን ለመጥቀስ፤

9 . ለምሳሌ የአፍሪቃ አንድነት ኮሚሽን ሊቀ መንበር የነበሩት ሚስስ ድላሚኒ ዙማ እንዲህ የመሰለ አመለካከት አላቸው፡፡ Jeggan Grey-Johnson, "Is the AU blinded by its own vision?", (Open Society Initiative for Southern Africa OSISA), April 8, 2015, <[http://www.osisa.org/openspace/regional/au-blinded-its-own-vision](http://www.osisa.org/openspace/regional/au-blinded-its-own-vision) > accessed on January 3, 2018 ከዚህ ጋር በተያያዘ የአፍሪቃ አገሮችን ለማዛመድና ለማወሃሃድ ተብለው ያለፉ ውሳኔዎችና የተነደፉ ዕቅዶች መኖራቸው ሊጠቀስ ይገባል፡፡የመጨረሻው የዚህ ዓይነት ውሳኔ ባለፈው ወር የአፍሪቃ ህብረት በኪጋሊ ስብሰባው ያሳለፈው "የአፍሪቃ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና" የተባለው ነው፡፡ የኪጋሊ ውሳኔ ከመወሰዱ በፊት የታተመ ቢሆንም የሚከተለው ፅሁፍ ጠቃሚ ነው፡፡ Talkmore Chidede, "The African Continental Free Trade Area (AfCFTA) and other African Union (AU) initiatives for economic integration", < https://www.tralac.org/discussions/article/12790-the-african-continental-free-trade-are… > accessed on March 22, 2018

10 በዚህ ፅሁፍ በደቡብ ሱዳን ልሂቃኖች መሃከል ስለኮንፌደረሽን ከተካሄዱት የፅሁፍ ክርክሮች ብዙ ሃሳቦች ወስጄ ተገቢውን ዕውቅና (ምስጋና) በመስጠት ተጠቅሜአለሁ፡፡

11 . Carl James Chol, "Mr. Malik Agar and Confederation", Pachodo.org, < https://pachodo.org/latest-news-articles/pachodo-english-articles/515-mr-malik-agar-a…> accessed on January 10, 2018; John A. Akec, "Confederation; A Better Tool for Good Neighborliness and Prosperous Relationship between Sudan and South Sudan", op. cit., John Apuruot Akec, "Why confederation in Post-Referendum Sudan is key to prosperous, stable, and good neighbourliness", Sudantribune.com, 18 November, 2010 <[http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=36978](http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=36978) > accessed on January 10, 2018

1. የኮንፌደረሽንን ራዕይ - በኢትዮጵያና ኤርትራ መሃከል ይሁን በአፍሪቃ ቀንድ ደረጃ - የሚያራምድ ሃያል ወይም በህዝቦቹ ተቀባይነት ያለው መሪ ይሁን ንቅናቄ የለም፡፡
2. ይህንን ጥያቄ በተመለከተ በኢትዮጵያና በኤርትራ ልሂቃን መሃከል በቂ መግባባት የለም፡፡
3. እያንዳንዱ አገር ከኮንፌደረሽኑ እንዴትና ምን ያህል ይጠቀማል በሚለው ጥያቄ ላይ አለመግባባት ያለ ይመስላል፡፡
4. አገሮቹ ወይም መንግስታቱ ስለሉዓላዊነታቸው - እያነሰ ቢመጣም - ገና እጅግ ቀናተኞች በመሆናቸው ለኮንፌደራላዊ ውህደት የተወሰነ ስልጣን ማስረከብ በሚለው ሃሳብ ይሰጋሉ፡፡
5. አገሮቹ መረጋጋት ይጎድልባቸዋል፡፡ ኤርትራ እጅግ የተጠላ መንግስት የሚቆጣጠራት የተንኰላሸች አገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ በዚሁ ጊዜ የተቃውሞ ንቅናቄዎች ያየሉባት፡ ጽናቱ የሚያስተማምን ህዝባዊ ተቀባይነት ያለው መንግስት ገና የሌላት፡ የመገነጣጠል አደጋም ያንዣበበባት አገር ናት፡፡
6. በአሁኑ ጊዜ በሁለቱ አገሮች - በተለያየ መጠን ቢሆንም - ከባድ የዲሞክራሲ ዕጥረት አለ፤ ለመረጋጋት ጉድለቱ ዋና ምንጭም ይህ ነው፡፡

እነዚህ ችግሮች ይኑሩ እንጂ ኮንፌደረሽን የሚፈለግና ለወደፊቱም የሚቻል ነው፡፡ እንድያውም ያሁኑ ወቅታዊ ዕውነታ ኮንፌደረሽን በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል አማራጭ የሌለው አስፈላጊ ዝምድና መሆኑን ነው የሚያመለክተው፡፡

ኮንፌደረሽን ለሁለቱ ህዝቦች በብዙ ረገድ ይጠቅማቸዋል፡፡

1. ኢትዮጵያም ኤርትራም የጎሳ ፖለቲካና ተዛማጅ ችግሮች ካስከተሉት ቀውስ የተነሳ የመገነጣጠል አደጋ አለባቸው፡፡ በኢህአዲግ ወሳኝ ሚና የተነደፈው ህገ-መንግስት በሚፈቅደው መሰረት ወያኔ ትግራይን አስገንጥሎ ከኢሳያስ መንግስት ጋር ሆኖ የትግራይ-ትግርኚ አገር የመመስረት የተደበቀ አጀንዳ እንዳለው ለዓመታት በተደጋጋሚ የተፃፈበት ነው፡፡ ይህ ወያኔ ኢትዮጵያን ለመግዛት በማይችልበት ሁኔታ ሲገባ የሚስበው ካርታ አሁንኑ ለብዙ ታዛቢ ግልፅ እየሆነ መጥቷል[12]፤ አጀንዳው በሚተገበርበት ጊዜ ኢትዮጵያም ኤርትራም ይገነጣጠላሉ ማለት ነው፡፡

---

12 . በዚሁ ጊዜ አንዳንድ ኤርትራውያንና የትግራይ ተወላጆች የትግራይ-ትግርኚን ዕቅድ በተለያየ መልክ እያራመዱት ነው፡፡ እነዚህ ካድሬዎች አንዳንድ ጊዜ "አግዓዝያን" በሚል ስም ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ይህንን አፍራሽ ዓላማ በማጋለጥ የEthiopian Semay አዘጋጅ ጌታቸው ረዳ ብዙ ፅሁፎች አበርክተዋል፡፡ ለምሳሌ እነዚህን ተመልከት፡፡ "ግብረ-መልሲ ንዶ/ር ሙሉወርቅን ገረኺዳን ደስታን"፡ togoruba.org 25 March 2018; ""ግብረ መልሲ ንዶ/ር ሙሉወርቅ ኪ/ማርያም" 2ይ ክፍሊ togoruba.org 06 April 2018. እንዲሁም የሚከተለውን ዕይ Al Mariam, "A Rejoinder to Seyoum Mesfin's call to Arms to the People of Tigray", Al Mariam's Commentaries, February 4, 2018 available online at http://almariam.com/2018/02/04/a-rejoinder-to-seyoum-mesfins-call-to-arms-to-the-p…; እንዲሁም የሚከተለውን የአክቲቪስት ነጋሲ በየነን ቃለ-መጠይቅ አዳምጥ Negasi Beyene , "Talk of 'Tigrai Secession' is Talk of the Idle, Not the Concern of the People of Tigrai, says Activist Negasi Beyene", ethiomedia.com March 5, 2018

ኮንፌደረሽን የመገነጣጠልን አደጋ በማስቆም ላይ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የሚቋቋመው ኮንፌደረሽን አቅጣጫው አንድነታዊ ነው፡፡ ጨርሰው በህግ የተለያዩ ሁለት አገሮች በኮንፌደረሽን መተሳሰር ሲጀምሩ ወደ አንድነት እየመጡ ናቸው፡፡ በሁለቱ አገሮች መሃከል የሚሰፍነው የፖለቲካ አየር የአንድነት ሆኖ በውስጣቸው ባለው የህዝቦች ወይም ብሄሮች ግንኙነት ላይም እንድምታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ አነጋገር ኮንፌደረሽኑ የብሄሮች ዝምድናን በተመለከተ አርአያነት ይኖረዋል፡፡ የመለያየትንና የመገንጠልን ስነ-አእምሮና አዝማሚያዎች እያዳከመ መቀራረብንና ወንድማማችነታዊ ዝምድናን ያበረታታል፡፡ ስለዚህ ኮንፌደረሽን ለሁለቱ አገሮች ቀጣይ ህልውና አስፈላጊ ነው ማለት ይቻላል፡፡

2. ሰላማዊ ግንኙነትን ያጠናክራል፤ ጥላቻን በመቆጣጠር ጦርነትን ሊያስወግድ ይችላል[13]፤
3. ሁኔታው በጠቅላላ ለመረጋጋት የሚመች ሆኖ፡ ለእድገት ተስማሚ ነው፤
4. በሁለቱም አገሮች የመንቀሳቀስና የመኖር ነፃነት ስለሚኖር፡ በድንበር ሰበብ ግጭት ሊመጣ ያለው ዕድል አነስተኛ ይሆናል[14]፤
5. ኮንፌደረሽን ለሁለቱም አገሮች ሰፊ ገበያ ያቀርብላቸዋል፤ የሚያመርቱትን ለመሸጥ ገበያ ያገኛሉ፤ ይህም ለዕድገት ጠቃሚ ነው[15]፡፡

ኮንፌደረሽን፡ ከሁለቱ አገሮች አልፎ በቀጠናው፡ እንዲያውም በአፍሪቃ አህጉር በጠቅላላ አዎንታዊ እንድምታ ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡ ኮንፌደረሽኑ በደንብ ስራ ላይ ከዋለ፡ ሁለቱን አገሮች ያበለፅጋል፡ ያሳድጋል፡፡ ይህም ሲሆን ልዓላዊነታቸው ይጠነክራል፡፡ በዚሁ ወቅት ብዙ የአፍሪቃ አገሮች በተግባር እንደገና ቅኝግዛት እየሆኑ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያና ኤርትራ በኮንፌደረሽን ተሳስረው በመጠንከር ለዓላዊነታቸውን በማውለብለብ ለአፍሪቃ ኩራት ተስፋና አብነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

፬

ስለ ኮንፌደረሽን በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን በኩል ከባድ የአመለካከት ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህን ችግሮችና ዕንቅፋቶች ከ10 ዓመት በፊት ባሳተምኩት መጠነኛ መፅሃፍ[16] በሰፊው ገልጫቸዋለሁ፡፡ በዚሁ ፅሁፍ ዋናዋናዎቹን አጠር አድርጌ እገልፃለሁ፡፡

በኢትዮጵያውያን በኩል ከሚሰተዋሉት ችግሮች አንዳንድ አብነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

---

13. Abdullahi Osman El-Tom, "Towards Confederation between Independent South and North Sudan", Sudan Tribune 12 July 2010, < http://sudantribune.com/spip.php?article35633 > accessed on January 3 2018
14 . ዝኒ ከማሁ
15 . Zechariah Manyok Biar, "Confederation for Sudan: Is it a good idea?", Sudan Tribune, June 4, 2019, <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=35572 > accessed on January 10, 2018
16 . Tesfatsion Medhanie, *Towards Confederation in the Horn of Africa: Focus on Ethiopia and Eritrea*, (Göttingen: Cuvillier Verlag 2009)

- ኤርትራ አንዴ መገንጠልን መርጣለች፤ በኮንፌደረሽን ይሁን በሌላ መልክ እንደገና መዛመድ አያስፈልገንም የሚሉ ኢትዮጵያውያን - ቁጥራቸው እያነሰ ቢመጣም - ገና አሉ። እንዲህ የመሰለ አመለካከት በመገንጠል የተቋጨውን የተወሳሰበ የኤርትራ ጉዳይ - በተለይ ስነ-ኣእምሮአዊ ጐድኑን - በሚገባ ያላጤነ ይመስለኛል። ጦርነት እኮ ደስ የሚል ነገር አይደለም[17]። አንድ ህዝብ የትጥቅ ትግል የሚያካሂደው ወዶ ሳይሆን ተገዶ ነው። የኤርትራን ንቅናቄ ያነሳሱት በአፄው ዘመንና ከዚያም በኋላ የተደረጉትን የፖለቲካ ስህተቶች ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

ብዙዎች እንዲህ አመለካከት ያላቸው፡ ሌሎችም፡ አስተዋይና አገር-ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ጨምሮ፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የወደብ ጉዳይ፡ በተለይ ዓሰብን በተናጠል፡ ያነሳሉ[18]። ለኔ እንደሚመስለኝ፡ አንዴ ኮንፌደረሽኑ ይጀመር እንጂ ይህ ጉዳይ አከራካሪ አይሆንም። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ያሉት አለመግባባቶች ኮንፌደረሽኑ ከተቋቋመ በኋላ የሚፈቱበት ዘዴዎች ይፈጠራሉ። ለነገሩማ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፋዊ ህግ መሰረት ዓሰብን ብቻ ሳይሆን ምፅዋንና ሌሎች ወደቦችን ለመጠቀም የሚያስችላት መብት አላት። ችግሩ ኤርትራ ውስጥ ይህንን መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጨዋ ጤነኛና ለህግ ተገዢ የሆነ መንግስት የሌለ መሆኑ ነው።

- ኤርትራ አንዲት ድሃ አገር ናት፤ እኛ ይችን አገር ማዳን የለብንም የሚሉም አሉ። አንዳንዱማ ኤርትራ ያልተሳካላት-አገር (failed state) ናት ይላል። እርግጥ ኤርትራ በአሁኑ ጊዜ ለህዝብዋ ስቃይ ናት። ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ ግን መታወቅ ያለባቸው ሁለት ነገሮች አሉ፡ 1. የወቅቱ የኤርትራ ችግር አስመራ ያለው መንግስት የፈጠረው ነው። የኤርትራ ህዝብ ታታሪና ሰራተኛ መሆኑ የታወቀ ነው። በ90ዎቹ መጀመርያ ታጥቆ ተነስቶ እንደነበረ ብዙ የተዘገበበት ነው። 2. ኤርትራ በአሁኑ ጊዜ የተንኰላሸች አገር መሆንዋን እቀበላለሁ። ይህ ሁኔታ ግን ኮንፌደረሽንን አላስፈላጊ ሳይሆን በበለጠ ጠቃሚና ተፈላጊ ነው የሚያደርገው። ለኢትዮጵያ የሚበጀው ኤርትራ ከዚሁ የድህነት እና የውድቀት ሁኔታ ብትወጣ ነው። ሁለቱ አገሮች ርዝመቱ ሺ ኪሎመትር የሆነ የጋራ ድንበር ያላቸው ጎረቤቶች ናቸው፤ ኤርትራ የተንኰላሸች ወይም ያልተሳካላት አገር ብትሆን ለኢትዮጵያ አደገኛ ነው። ኤርትራ ከተንኰላሸች ህዝብዋን በሀይል የምታሽቆጠቁጥና የምታሰቃይ ግፈኛ ሥርዓት (fierce state)[19]፡ብቻ ሳይሆን ቀጠናውን የሚያውኩ ወረበሎች እምብርትም ልትሆን ትችላለች። ስለዚህ ኮንፌደረሽኑ ኤርትራን ከመንኰላሸት ቢያድናት ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ነው።

- ሌላው ነጥብ ደግሞ ኮንፌደረሽን ኤርትራን ነው እንጂ ኢትዮጵያን አይደለም የሚጠቅመው የሚል ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ90ዎቹ መጀመርያ ላይ ኤርትራ

17 . ደቡብ ሱዳንን በተመለከተ ዶክ. ፈራንሲስ ደንግ ይህንን ነጥብ አስምረዉበታል። Francis M. Deng, “Prospects for Reconciling Self-Determination with Unity in Sudan”, op. cit.

18. ለምሳሌ የሚከተለውን ዕይ። ዶ/ር ያዕቆብ ሀይለማርያም “አሰብ የማን ናት? የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ“ (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ. ም.)

19 . ደቡብ ሱዳንን በተመለከተ ስለዚህ ፅንሰ-ሃሳብ የሚከተለውን ዕይ። Hamid Eltgani Ali, “How to govern Sudan: A questv for confederation”, Sudan Tribune January 11, 2010 <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=33735 > accessed on January 3, 2018

ኢትዮጵያን እንደበዘበዘች ይጠቀሳል፡፡ በዚያን ጊዜ የኢሳያስ መንግስት ከኢትዮጵያ ብዙ ሃብት እንደዘረፈ ሀቅ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ መታወቅ ያለባቸው መሰረታዊ ነገሮች አሉ፡፡ 1. በዚያን ጊዜ ይሁን ከዚያ በኋላ በሁለቱ አገሮች ኮንፌደረሽን አልነበረም፡፡ ስለዚህ የተደረገውን ብዝበዛ የኮንፌደረሽን አብነት አድርጎ ማቅረብ ትክክል አይደለም፤ ቅን አቀራረብም አይመስለኝም፡፡ 2. ቅሚያው እንዲፈጸም ያስቻለ መለስና ኢሳያስ ሲመሩት የነበረው በወያኔና በሻዕቢያ መካከል የነበረው ሽርክና ወይም ጓዳዊ ዝምድና ነው፡፡ ከኮንፌደረሽን ጋር የሚያገናኝ ምንም የለውም፡፡ የማቀርበው ያለሁት የኮንፌደረሽን ሃሳብ በአገሮቹና በህዝቦቹ እኩልና ፍትሃዊ ዝምድና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

እርግጥ ነው፣ ከኮንፌደረሽኑ በተወሰነ ረገድ አንዳቸው በበለጠ ሊጠቀም ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ግን ችግር አይደለም በመሰረቱ ሌላውም የሚጠቀም እስከሆነ ድረስ፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ በበለጠ ብትጠቀም ችግር የለውም፤ ነገር ግን ኤርትራም ያነሰም ቢሆን መጠቀም አለባት፡፡ ችግር የሚኖረው አንዳቸው የሚጠቀም፣ ሌላኛው ደግሞ የማይጠቀም ሲሆን ነው፡፡

- አንዳንዶቹ ደግሞ የባድመን ጦርነትንና ሌሎች የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ያበላሹ ችግሮችን በማስታወስ ኤርትራ ጠበኛና ወራሪ ናት፣ ስለዚህ ከኤርትራ ጋር ኮንፌደረሽን አያስፈልግም ይላሉ፡፡ ክሱ ፈጽሞ መሰረተ-ቢስ ባይሆንም፣ ኮንፌደረሽንን ላለመቀበል ፈጽሞ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

መረሳት የሌለበት አንድ ነጥብ አለ፡፡ ኮንፌደረሽኑ የሚጀመረው አሁን ሳይሆን በሁለቱ አገሮች ዲሞክራሲያዊ ወይም ህዝብ የተቀበለው መንግስት ሲቋቋም ነው፡፡ አንዴ በኤርትራ ህዝባዊ መንግስት ከተቋቋመ አገሪቱ ቢያንስ ለራሷ ጥቅም ስትል ከጎረቤቶችዋ ጋር ሰላማዊና የትብብር ዝምድና እንደምትመርጥ ጥርጥር የለውም፡፡

በኤርትራውያን በኩልም የተሳሳቱ አመለካከቶች አሉ፡፡ ከዋናዎች አንዳንዱ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ብዙ ኤርትራውያን በፌደረሽንና ኮንፌደረሽን መሃል ያለውን ልዩነት አያውቁም፡፡ ስለዚህ ልክ ፌደረሽንን እንደሚቃወሙ ኮንፌደረሽንንም ይቃወማሉ፡፡ አስታወሳለሁ፣ ስለ ኮንፌደረሽን መፅሃፍ ባሳተምኩበት ወቅት ብዙ ኤርትራውያን አሁን ደግሞ ፌደረሽንን እንቀበል እያለን ነው ብለው ረግመዉኛል፡፡ በነገራችን ላይ ፌደረሽንን የሚቃወሙት "ፌደረሽን" ሲባል የሚያስታውሱት ያ በአፄ ሃይለስላሴ ዘመን የነበረውንና የፈረሰውን አውቶኖሚ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ኮንፌደረሽን ከፌደረሽን የተለየ መሆኑን ማስተማር ሊኖርብን ነው፡፡

- አንዳንድ ኤርትራውያን ደግሞ በኮንፌደረሽን ዝምድና ኢትዮጵያን ልናምናት አንችልም፤ ድሮ ፌደረሽኑ እንዲፈርስ እንዳደረገች ሁሉ አሁንም ከኤርትራ ጋር ስትነፃፀር ትልቅና ሀያል በመሆንዋ ኤርትራን ልትውጣት ትችላለች ይላሉ፡፡ ይህ ፍርሃት መሰረተ-ቢስ ነው፡፡ የድሮውን ፌደረሽን በማፍረስ ምን ያህል እንደከሰሩ ኢትዮጵያውያን

ያውቃሉ፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ሁሉን የሚወክል ህዝባዊ መንግስት ስታቋቁም ከኤርትራ ጋር የሚኖራትን በህግ የተመሰረተ የኮንፌደረሽን ቃል ኪዳን ለማክበር ብቃት እንደሚኖራት ጥርጥር የለውም፡፡

- ኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላታችን ናት ብለው የሚከራከሩ አንዳንድ ኤርትራውያንም አሉ፡፡ ይህ አመለካከታቸው በጣም የተሳሰተ ነው፡፡ በፖለቲካ እንኳንስ እንደ ኢትዮጵያና ኤርትራ በመሰሉት ወንድማማች ህዝቦች፣ በታሪክና በባህል በተራራቁ ሀገሮች መሀከልም ቢሆን ቋሚ ወይም ነዋሪ ጥላቻ የሚባል የለም፡፡ እንዲያውም ጠላቶች የነበሩ አገሮች ወዳጆችና ተባባሪዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ በታሪክ ብዙ ጊዜ ታይቷል፡፡ የፈረንሳይና የጀርመን ታሪክና ያሁኑ ዝምድና አንድ አብነት ነው፡፡

- ታሪክን በተመለከተ ብዙ ኤርትራውያን የተሳሳተ አስተሳሰብ አላቸው፡፡ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን - በተለይ የደጋው ኤርትራውያን - ረጅም የጋራ ታሪክና የተሳሰረ ባህል እንዳላቸው አያውቁም ወይም ይክዳሉ፡፡ ሌላውስ ይቅርና ኤርትራውያን ለኢትዮጵያ ነፃነትና ዕድገት ያደረጉት አሰተዋፅኦ ምን ያህል ታላቅ መሆኑን እንኳን አያውቁም፡፡ ይህ ከባድ ጉድለት ነው፡፡ የኤርትራ ልሂቃን ይህንን ጉድለት ለማረም ብዙ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

- በኤርትራውያንና በኢትዮጵያውያን በኩል ባሁኑ ጊዜ የሚስተዋሉ ስነ-አእምሮአዊ ችግሮች አሉ፡፡ ኤርትራውያን - በተለይ እነዚያ የኮንፌደረሽንን ትርጉም የማያውቁ - ከዚህ ሁሉ ጦርነት፣ ሞትና ኪሳራ በኋላ እንዴት ከኢትዮጵያ ጋር በኮንፌደረሽን ይሁን በፌደረሽን እንዛመዳለን! ይላሉ[20]፡፡ በኢትዮጵያውያን በኩልም - አንዳንድ "አክራሪዎች" የሚባሉትን ጨምሮ - ኤርትራውያን እኮ አንፈልጋችሁም ብለው ሄደዋል፤ አሁን ኤርትራ ያልተሳካላት አገር በመሆንዋ ከፍቷቸው ከኢትዮጵያ ጋር በኮንፌደረሽን መዛመድ ቢፈልጉ መቀበል የለብንም ይላሉ፡፡

እነዚህ አመለካከቶች ትክክል አይደሉም፡፡ የኤርትረያኖቹ አመለካከት ያለፈውን ብቻ የሚያስታውስ፣ ባለፈው ሁኔታ የሚገዛ፣ ለራስ ጥቅም የማያገለግል፡ እንዲያውም የሚጎዳ ነው፡፡ ነገሩ መታየት ያለበት በቁጭትና በስሜት ሳይሆን ከጥቅም አኳያ ነው፡፡ የሚፈለገው ወደፊት ያቀና ለሁለቱ አገሮች የሚጠቅም አካሄድና ዝምድና ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት ብዙ ጉዳት ደርሶብናል ብሎ አሁን ለሁላችን የሚጠቅመውን ዝምድና አንቀበልም ማለት ሞኝነት ነው፡፡ የኢትዮጵያኖቹም እንደዚሁ ስህተት ነው፡፡ ማንኛውም ህዝብ በተሞክሮና በሂደት ተምሮ አመለካከቱን ሊለውጥና ሊያሳድግ ይችላል፡፡ አስተዋይ የፖለቲካ ሰዎች ተለያይቶ እንደገና መተሳሰር ያልተለመደ እንዳልሆነ ነው የሚመሰክሩት፡፡ እንዲያውም ተለያይቶ እንደገና ወደ አንድነት ጎዳና መምጣት የመገንጠሉ ሂደት ቅጥያ ሆኖ

20 . እንዲህ ዓይነቱ ስሜት ባንዳንድ የደቡብ ሱዳን ልሂቃንም የነበረ ይመስላል፡፡ ለምሳሌ ይህንን ተመልከት፡፡ James Okuk, "Confederation for Southern Sudan a Betrayal to Self-Determination", Pachodo.org, January 17, 2008 < https://pachodo.org/latest-news-articles/pachodo-english-articles/516-confederation-fo…> accessed on January 10, 2018

የሚገኝበት ሁኔታ አለ፤ በሌላ አነጋገር፡ መገንጠል ራሱ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ሂዶ-ሂዶ የአንድነትን መንፈስና ፍላጎት ሊወልድ ይችላል[21]፡፡

፰

ኮንፌደረሽን እንዲሁ በችኰላ በማንኛውም ሁኔታና ጊዜ የሚቋቋም ነገር አይደለም፡፡ አስቀድመው መሟላት ያለባቸው ነገሮች አሉ[22]፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ኮንፌደረሽን ዝምድናው የሚመለከታቸው ህዝቦች ትርጉሙ ገብቶዋቸው በሙሉ ፈቃድ የሚቀበሉት መሆን አለበት፡፡ ጉዳያችንን በሚመለከት የኢትዮጵያና የኤርትራ ዜጎች ኮንፌደረሽን ምን ማለት እንደሆነና እንዴትስ እንደሚጠቅማቸው መጀመርያውኑ መረዳት ያስፈልጋቸዋል፡፡

ይህ እንዲሆን በሁለቱ አገሮች ነጻ ውይይትን የሃሳብ መለዋወጥን እና ለፖለቲካዊ ዓላማ መደራጀትን የሚፈቅድ ሁኔታ ወይም የፖለቲካ ሁዋ መኖር አለበት፡፡ ይህ ማለት በሁለቱ አገሮች የበለጸገም ባይሆን በመሰረቱ ዲሞክራስያዊ የሆነ ስርዓት መኖር አለበት ማለት ነው[23]፡፡ ይህንን ስርዓት በሚመለከት ትንሽ ማብራርያ አስፈላጊ ነው፡፡

ካሁን በፊት በአንድ ጽሁፌ እንደገለጽኩት ለዚህ ጉዳይ ይሁን ወይም በጠቅላላው ለኢትዮጵያና ለኤርትራ - እንዲያውም ለማንኛውም አፍሪቃዊ አገር - የሚበጅ ስርዓት የብሄራዊ አንድነት መንግስት (Government of National Unity) የሚባለው ነው፡፡ ይህ ማለት ያሉት እንጋፋ የፖለቲካ ቡድኖች ላላቸው ድጋፍ ተመጣጣኝ በሆነ መልክ ተወክለው የሚሳተፉበት ሰፊ ጣምራ መንግስት ማለት ነው፡፡

በኢትዮጵያና በኤርትራ እንዲህ ዓይነት ስርዓት ሲሰፍን ህዝቦቹ የኮንፌደረሽንን ጥያቄ በተመለከተ ሃሳባቸውንና ፍላጐታቸውን በሙሉ ነጻነት ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ ኮንፌደረሽን እንዲህ በመሰለ ሁኔታ ሲከሰት አጥጋቢ፡ አስተማማኝ እና በውህደት አቅጣጫ የሚያድግ ይሆናል፡፡

የኮንፌደረሽንን ሂደት ለማስተጋባት መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎችና ቅደም-ተከተላቸው ምን እንደሚመስል መጠነኛ ሃሳብ በማቅረብ መልእክቴን ማጠቃለል እወዳለሁ፡፡

1. በኢትዮጵያም በኤርትራም ባሁኑ ወቅት ሁኔታዎቹን ሊያረጋጋ የሚችል ተቋም እንጋፋዎቹን የፖለቲካና የሲቪል ህብረተ-ሰብ ቡድኖች ያካተተ የሽግግር መንግስት

21 . John A. Akec, “Confederation; A Better Tool for Good Neighborliness and Prosperous Relationship between Sudan and South Sudan”, op. cit

22 . ደቡብ ሱዳንን በሚመለከት የሚከተለውን ዕይ፡፡ John A. Akec, “South Sudan self-determination is the gateway to an enduring and stable united Sudan”, Sudan Tribune, <http://sudantribune.com/spip.php?article33137 > accessed on January 11, 2018

23. University of Pretoria, “Supranationalism in the African context; A critical look at past and present attempts at building supranational organizations in Africa”, op. cit. p. 115

ነው፡፡ ግቡ ምን እንደሆነ በትክክል አልታወቀም እንጂ በኢትዮጵያ አሁን የለውጥ ሂደት የተጀመረ ይመስላል፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአገር ውስጥም በውጭም ከፍ ያለ ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ የዶክ. ዐቢይ አስተዳደር የለውጡ ሂደት እንዲቀላጠፍና የሚፈለገው የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ብልህና ቆራጥ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ኤርትራ ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን ጭፍን አምባገነንነት ነውና ከበድ ባለ ትግል ካለፍን በኋላ ነው የሽግግር መንግስት የሚቋቋመው፡፡

2. ከዚያ ቀጥሎ በይዘቱ ከብሄራዊ አንድነት መንግስት፡ ከዲሞክራሲ እና ከአድማሳዊ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ ጋር የሚጣጣም ህገ-መንግስት ተነድፎ በህዝብ ይፀድቃል፡፡ በህገ-መንግስቱ መሰረት ምርጫ ተካሂዶ መለያው የብሄራዊ አንድነት መንግስት የሆነ ስርዓት አገሮቹን ያስተዳድራል፡፡

3. የሁለቱ አገሮች ህገ-መንግስታትና ሌሎች ህጎች እንዲሁም መሰረታዊ ፖሊሲዎች የሚጣጣሙ ወይም ተመሳሳይ እንዲሆኑ ይደረጋል[24]፡፡

4. ሁኔታው በተመቸ ጊዜ መንግስታቱ የኮንፌደረሽን መቋቋምን በተመለከተ ድርድርና ተዛማጅ ሂደቶች ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለኮንፌደረሽን ትርጉምና ሊገኙ ስለሚችሉት ጥቅሞች የሁለቱ አገሮች ህዝብ አስፈላጊው ግንዛቤ እንዲኖረው ህዝባዊ ውይይት - ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን አብረው የሚሳተፉበትን ጨምሮ - እንዲደራጅና እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

5. ኮንፌደረሽንን በማቋቋም ላይ በሁለቱ አገሮች ሪፈረንደም ይካሄዳል፤ ውጤቱ ሃሳቡን የሚደግፍ ሲሆን የኮንፌደረሽኑ ጉዞ ይጀመራል፡፡

6. ኮንፌደረሽኑ ዕውነታው በሚፈቅደው ከፍተኛ የጋራ ተቋማትና የጠበቀ ግኑኝነት እንዲኖሳ ተደርጎ ይነደፍና የመጀመርያው ኮንፌደረሽን ዕድሜ 5 ዓመት ይሆናል፡፡

7. *አምስት ዓመት ሲያልቅ እንደገና ሪፈረንደም ይካሄዳል፡፡ በ5ቱ ዓመታት ዝምድናው ምን ያህል የህዝቦቹን ህይወት ለማሳደግ እንዳገለገለ ይገመገማል፡፡ ኮንፌደረሽኑ አጥጋቢ ፍሬ ሰጥቷል ከተባለ፡ ይዘቱ ከፍ እንዲል ተደርጎ በሁለቱ አገሮች ህዝቦች ነፃ ፍላጎት ይሻሻላል፤ ይህ ማለት ኮንፌደረሽኑ አገሮቹን በበለጠ በሚያቀራርብ መልክ ይታደሳል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ኢያለ ኮንፌደረሽኑ በውህደት አቅጣጫ ያድጋል፡፡*

*ይህ ቅደም ተከተል በጎና ደግ በሆነ አመለካከት የተመሰረተ ነው፡፡ ካለበለዚያ ሁኔታው ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው፡፡ ችኮላን ማስወገድ አለብን፡፡ በቅርብ ታሪካችን በችኮላ የተወሰዱ አላስፈላጊ እርምጃዎች ገና ኢያጉላላን ያለውን ችግር ፈጥረውብናል፡፡*

---

24. ይህንን ለሚመስል ሃሳብ የሚከተለውን ተመልከት፡፡ Jeggan Grey-Johnson, “Is the AU blinded by its own vision?”, op. cit.

*የኮንፌደረሽን ሃሳብ ብዙ ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለኤርትራ ህዝብ በጎ የማይመኙ ጠላቶች አሉት፡፡ በደቡብ ሱዳን ጉዳይ እንደታየው ጠባብ አመለካከት ያላቸው አንዳንድ ተንቀሳቃሾች መገንጠልን ነፃነት ብለው ወደሱ፤ ኮንፌደረሽንን ደግሞ ባርነት ብለው ኮነኑ*[25]*፡፡ እንዲህ የመሰለ አሉታዊ አመለካከት ባባከለው ሁኔታ ደቡብ ሱዳን ተገንጥላ አሁን ጨለማ የነገሰባት አገር ሆናለች፡፡*

*በኤርትራውያን በኩልም እንደዚሁ ኮንፌደረሽንን ተቀባይነት እንዳያገኝ ለማድረግ የሚጥሩ አልታጡም፡፡ ከነርሱ አንዱ በቅርብ ጊዜ በስዊድን አገር በትግርኛ በሰጠው ቃለ-መጠይቅ አንዳንድ ዜጎች የሚያቀርቡትን የኮንፌደረሽን ሃሳብ “ዓዘፍዘፍ” (ማለት መዋዠቅ ወይም የማይረባ ንግግር) ብሎ ለማጣጣል ቃጥቷል፤ ከዚያም አልፎ ኤርትራን በተመለከተ ኮንፌደረሽንን እንደ “ባርነት” አድርጎ አቅርቦታል፡፡ ሰውዬው የኮንፌደረሽን ትርጉምና ጥቅም ጠንቅቆ የሚያውቅ የዕድሜና የዕውቀት ባለፀጋ ነው፡፡ ይህንን ውሸት ማራመድ - ትክክለኛ ዓላማው ምን ይሁን ምን - ከርሱ የማይጠበቅ አደገኛና እጅጉን የሚያሳዝን ተግባር ነው፡፡*

*እንዲህ የመሰሉ ሃላፊነት የማይሰማቸው ምሁራን ህዝቡን ግራ የሚያጋባ ውሸት እያሰራጩ መሆናቸውን አውቀን ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ግልፅ ነው፡፡ ለምሳሌ አስቀድሜ እንዳልኩት ኮንፌደረሽኑ በየጊዜው እየታደሰ ያድጋል፤ ሁለቱ አገሮች ይቀራረባሉ፤ እሰከ ፌደረሽን ሊጓዙ ይችላሉ፤ የሂደቱ የመጨረሻው ግብ ፌደረሽን ነው ተብሎ ግን አስቀድሞ አይታወጅም፡፡ ማንኛውም የመቀራረቡ ዕድገት ተግባራዊ ዝምድናው በሂደት የወለደው ሆኖ ነው መምጣት ያለበት፡፡ ግቡ ፌደረሽን ነው ተብሎ ከታወጀ ጠላቶቻችን ይበዘብዙታል፤ ህዝቡም ይበረግጋል፤ ኮንፌደረሽኑ ተቃውሞ ገጥሞበት ሊፈርስ ይችላል፡፡*

*በጥንቃቄ ከተተገበረና አካሄዱ ካማረ፡ ማለት ህዝቦቹን በበለጠ ካረካ፡ ካቀራረበ፡ ካፋቀረና ካስተማመነ ኮንፌደረሽኑ በውህደት አቅጣጫ ያለማቋረጥ ያድጋል፡፡ በህዝቦቹ ሙሉ ፈቃድ መጨረሻው ፌደረሽን ሊሆን ይችላል፡፡*

25 . John A. Akec, “To confederate or not to confederate isa matter of strategy”, op. cit.

# ዋቢ ጽሁፎች

John A. Akec, “To confederate or not to confederate isa matter of strategy”, Sudan Tribune, Septemvber 14, 2010, <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=36261 >accessed on January 10, 2018, ;

John A. Akec, “Confederation; A Better Tool for Good Neighborliness and Prosperous Relationship between Sudan and South Sudan”, *UNISCI Discussion Papers*, Nr. 33, October 2013 (Madrid Spain), p. 158 <http://www.redalyc.org/articulo.oa?id=76728723011 >;

John Apuruot Akec, “Why confederation in Post-Referendum Sudan is key to prosperous, stable, and good neighbourliness”, Sudantribune.com, 18 November, 2010 <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=36978 > accessed on January 10, 2018

John A. Akec, “South Sudan self-determination is the gateway to an enduring and stable united Sudan”, Sudan Tribune, < http://sudantribune.com/spip.php?article33137 accessed on January 11, 2018

John A. Akec, “A call for renewable confederation in post 2011 Sudan”, Sudan Tribune June 8, 2010 <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=35326> accessed on January 10, 2018

Hamid Eltgani Ali, “How to govern Sudan: A questv for confederation”, Sudan Tribune January 11, 2010 <http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=33735> accessed on January 3, 2018

Abdullahi Ahmed An-Na’im, “Third World Perspectives”, in Elizabeth Ferris (ed), *The Challenge to Intervene: A New Role for the United Nations,* (Uppsala: Life & Peace Institute, 1992), p. 145

Negasi Beyene , “Talk of ‘Tigrai Secession’ is Talk of the Idle, Not the Concern of the People of Tigrai, says Activist Negasi Beyene”, ethiomedia.com March 5, 2018

Zechariah Manyok Biar, “Confederation for Sudan: Is it a good idea?”, Sudan Tribune, June 4, 2019,

<http://sudantribune.com/spip.php?iframe&page=imprimable&id_article=35572> accessed on January 10, 2018

Talkmore Chidede, "The African Continental Free Trade Area (AfCFTA) and other other African Union (AU) initiatives for economic integration", <https://www.tralac.org/discussions/article/12790-the-african-continental-free-trade-are…>, accessed on March 22, 2018

Carl James Chol, "Mr. Malik Agar and Confederation", Pachodo.org, <https://pachodo.org/latest-news-articles/pachodo-english-articles/515-mr-malik-agar-a…>, accessed on January 10, 2018;

Francis M. Deng, "Prospects for Reconciling Self-Determination with Unity in Sudan", (Khartoum,: Symposium on Unity and Self-Determination, November 2, 2009) <http://www.un.org/en/preventgenocide/adviser/pdf/SAPG%20statement%20in%20Khartoum.%20Nov%2009.pdf >accessed on March 7, 2018

Abdullahi Osman El-Tom, "Towards Confederation between Independent South and North Sudan", Sudan Tribune 12 July 2010, <http://sudantribune.com/spip.php?article35633>, accessed on January 3 2018

Jeggan Grey-Johnson, "Is the AU blinded by its own vision?", (Open Society Initiative for Southern Africa OSISA), April 8, 2015, <http://www.osisa.org/openspace/regional/au-blinded-its-own-vision > accessed on January 3,

Al Mariam, "A Rejoinder to Seyoum Mesfin's call to Arms to the People of Tigray", Al Mariam's Commentaries, February 4, 2018 < http://almariam.com/2018/02/04/a-rejoinder-to-seyoum-mesfins-call-to-arms-to-the-p…; l>

Tesfatsion Medhanie, *Towards Confederation in the Horn of Africa: Focus on Ethiopia and Eritrea*, (Göttingen: Cuvillier Verlag 2009)

James Okuk, "Confederation for Southern Sudan a Betrayal to Self-Determination", Pachodo.org, January 17, 2008 <https://pachodo.org/latest-news-articles/pachodo-english-articles/516-confederation-fo…> accessed on January 10, 2018

Mahmoud A. Suleiman, "Confederal System for Sudan", Sudan Tribune, January 8, 2008 < http://sudantribune.com/spip.php?page=imprimable&id_article=25592> accessed on Janury 10, 2018

University of Pretoria, "Supranationalism in the African context; A critical look at past and present attempts at building supranational organizations in Africa", <https://repository.up.ac.za/bitstream/handle/2263/28573/02chapter3.pdf?sequence=3>

**ያዕቆብ ሀይለማርያም፡ "አሰብ የማን ናት? የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ"** (**አዲስ አበባ፣** 2003 **ዓ. ም.**)

**ጌታቸው ረዳ፡ "ግብረ-መልሲ ንዶ/ር ሙሉወርቅን ገረኺዳን ደስታን"፡** togoruba.org 25 March 2018;

**ጌታቸው ረዳ፡ ""ግብረ መልሲ ንዶ/ር ሙሉወርቅ ኪ/ማርያም" 2ይ ክፍሊ** togoruba.org 06 April 2018